ስለ በደለኞች ሊያቀርቡል መና

...አዝ.....

አሳታውያኑ ሲራፌል ኪሩቤል

ሊነኩት ያልቻሉት የአሳቱን ነበልባል

አንቺ ግን አቀፍሽው ሳምሽው በከንፈርሽ

ከፍጥረት ለይቶ ፍፁም ስላፀናሽ

...አዝ.....

ማርያም ሆይ ስለዚህ እንወድሻለ

አንቺን ተማፅነናል እንድታማልጅን

ዘወትር እጆችሽ ተዘርግተዋልና

ስለበደለኞች ሊያቀርቡል መና

የተወደደ ቀን

የተወደደ ቀን የተወደደ ዓመት

ወደ አባቴ መቅደስ የተመለስኩበት

የአንባር ቀለበቴን የተሸለምኩበት

የተወደደ ዓመት

አዝ

አምሽቶ የመጣ አይገባም አትበሉ/2/

አባከኖ የመጣ አይገባም አትበሉ/2/

ፍቅር ስለሆነ እግዚአብሔር ለሁሉ/2/

ልጅ ቤቱን ይወርሳል እንደ ተስፋ ቃሉ/2/

አዝ

ከናዝሬት መልካም ሰው አይወጣም እያሉ/2/

ፊሊፖስ ናትናኤል ይነጋገራሉ/2/

አድርጉልና ውሃ ውን ወይን/2/

ዛሬም ለውጦኛል ወስዶታል ልቤን /2/

አዝ

አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር 

እኔ ነኝ አላማው እኔ ነኝ ሃሳቡ/2/

አባቴ ፍቅር ነው የሚራራ ልቡ/2/

ዘጠና ዘጠኙ ታምነውለት እያለ/2/

አንዱን ይፈልጋል ወዴትነህ እያለ/2/

አዝ

ሁሉን አይቻለው ሁሉን መርምሬያለው/2/

ዓለም ካንተ ሌላ እንደ ሌለ አቃለው/2/

ለማይለወጥ አባትነትህ ወዳጅነትህ

ጠፍቼስ መለስ አየውት ልጅህን/2/

#አዝ

ድንጋይ ያሸከመን ውሃ ተሸከመ

ለእኛ ቀን ወጣልን ለእርሱ ግን ጨለመ

ገዳይ ቢዘገይም ሟች በመገስገሱ

ፈረሰኛ ውሞተ እስከ ነፈረሱ(፪)

#አዝ

ቢመስለንም ሌቱ ፍፁም የማይነጋ

ተቆልፎ የሚቀር በሩ እንደተዘጋ

እርሱን ተስፋ አድርገው ባመንክበት ጽና

ቀን አለው እግዚአብሔር ያደርግሃ ልቀና(፪)

እንዲህ በአራት ነጥብ

እንዲህ በአራት ነጥብ ሊዘጋም ዕራፉ

እግዚአብሔር ሲያሸንፍ የእርሱ ሆኖ ሰልፉ

መልካም ለመናገር አፉ ባይታደል

ይህን እስኪያይ ጠላት ምናለ ዝምቢል(፪)

መልካሙን ደብቆ ክፉን እያሳየ

ይለኝ ነበር ጠላት እግዚአብሔር ዘገየ

ግን ሁሉን በጊዜው ውብ አድርጎ ሲሰራ

አፍሯል ለዘላለም ደንቆት የእርሱ ስራ(፪)

#አዝ

በቃ ልጅ የለህም አትወልድም ሳራ

ላይሰማህ እግዚአብሔር ቆመህበት ጣራ

እያለኝ ጠላቴ መስሎት ያሸነፈ

ይስሐቅ ተወለደ ያቀንም አለፈ(፪)

#አዝ

ፍፃሜዬን ሳያይ ገና ከጅምሩ

ጠላት በእርሱ ግምት ብዙ መናገሩ

አስብሎታል ቴቄል ተቀይሮ ስሙ

የዘገየ መስሎ ጌታ በመቅደሙ(፪)

ተክለአብ ነውና

ተክለ አብ ነውና መጠሪያ ስያሜህ

የእግዚአብሔርያን ተክብር የስም ትርጓሜ

ተክለሐይማኖት ብዬ ስምህን እጠራለው ደግሜ ደግሜ

ክርስቶስ ኢየሱስ ፀጋን ስለሰጠህ

ትባርከናለህ በብርሃን መስቀልህ

ለእኛ ለልጆችህ ፈጥነህ ትደርሳለህ

በነፍስም በስጋ ታማልደናለህ

ተክለወልድ ነውና መጠሪያ ስያሜህ

የወልደ እግዚአብሔር ተክልየስ ምህትር ጓሜ

ተክለ ሐይማኖት ብዬ ስምህን እጠራለው ደግሜ ደግሜ

ኃያሉ እግዚአብሔር ቃል ስለገባለት

ያኸው በፀበሉ ያደርጋል ታምራት

ማንም አፍሮ አያውቅም የመጣ ወደርሱ

በደስታ ይሄዳል ተገኝቶለት መልሱ

አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር 

ተክለ መንፈስ ቅዱስ መጠሪያ ስያሜህ

የመንፈስ ቅዱስ ተክል የስምህ ትርጓሜ

ተክለ ሐይማኖት ብዬ ስምህን እጠራለው ደግሜ

ደግሜ

የዋድቅ ሰው ዋጋው ከቶ አይጠፋምና

ሲያበራ ይኖራል ሁል ጊዜ እንደፋና

እኛም በእርሱ ታምነን ስሙን እንጠራለን

ገድሉን ታምራቱን እንመሰክራለን

ተክለ አብ ተክለ ወልድ ተክለ መንፈስ ቅዱስ

ተክለ እግዚአብሔር የተለየ ህቅዱስ

ባለመቶ ፍሬ ተክለሐይማኖት ሆይ ስምህን ላወድስ

የፅድቅንም መንገድ ኖሮ ስላለፈ

ፀጋ በረከትን ለእኛም አተረፈ

ወንጌልን በህይወት ስላስተማረን

ትዘከረዋለች ቤተክርስቲያን

ተክለ አብ ተክለ ወልድ ተክለ መንፈስ ቅዱስ

ተክለ እግዚአብሔር የተለየህ ቅዱስ

ባለመቶ ፍሬ ተክለሐይማኖት ሆይ ስምህን

አክሊለ ፅጌ

አክሊለ ፅጌ ማርያም አክሊለ ፅጌ

አክሊ ለፅጌ ማርያም አክሊ ለፅጌ

ስሟ ማርያም ነው አክሊለ ፅጌ

የጌታ እናት"

እናት አባቷ"

ያወጡላት"

ከምድርማር"

ከሰማይያም"

ብለውሰየሟት"

ድንግል ማርያምን"

አዝ.....

የስሟ ጣህም አክሊ ለፅጌ

ከማርይ በልጣል"

እንደሷያለ"

ከየትይገኛል"

የፍቅርመዝገብ"

ነቅህ የሌለባት"

ለክብሯ ወደር"

ማን አግኝቶላት"

አዝ.....

የከበረ ዘውድ አክሊለ ፅጌ

የወርቅ ሙዳይ"

የሽቱ ብልቃጥ"

የነፍሴ ሲሳይ"

ከጥፋት ውሀ"

ኖህ የዳነብሽ"

የሰላም መርከብ"

ቤቱ አንቺነሽ"

አዝ.....

በቤተ መቅደስ አክሊ ለፅጌ

ስትኖር ተመርጣ"

ምግቧን ይዘላት"

ፋኑኤል መጣ"

አስራ አምስት ዓመት"

ሲሆናት ድንግል"

በገብርኤል ብስራት"

ተፀነሰ ቃል"

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ መዝሙር □□:

ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን

ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን{፪}

ለታላቁ ክብር ለዚህ ያበቃን

ከሞት ወደ ህይወት ላሸጋገረን

የሰማዩን መንግስት እርስቱን ለሰጠን

ከጨለማው አውጡቶ ብርሃን ያሳየን

ለዚህ ድንቅ ውለታ ምስጋና ያንሰዋል

በእርሱ ደስ ይበለን ክብር ይገባዋል

ከአለት የፈለቀ ውሃ ጠጥተናል

ሰማያዊ መና አምላክ መግቦናል

ፍቅር የበዛ ነው ምን ልክፈል ጌታ

ስምህን ላመስግነው ከጥዋት እስከ ማታ

በቃዲስ በረሃ ምንም በሌለበት

በኤርትራ ባሕር ወጀብ የበዛበት

ለእርሱ መንገድ ዓለው ከቶ ምንተሰኖት

ልባቹ አይፍራ በፍጹም እመኑት

በባርነት ሳለን በድቅድቅ ዓለም

ብርሃንን አገኘን በድንግል ማርያም

ያጣነው ሰላም ዛሬ አገኘን

እጅግ ደስ ይበለን በእመቤታችን

የሃናና የእያቄብ የእምነታቸው ፍሬ

በእግዚአብሔር ፍቃድ ተወለደች ዛሬ

የእያቄብ ስለቱ የሃና እምነት

ለምኝልን ለኛም ኪዳነምህረት

ሰዎች እንዘምር

ሰዎች እንዘምር ላምላካችን

ከሞት ላወጣን ላዳኛችን

እናመስግነው እንዳቅማችን

ምህረትለሰጠን ለነፍሳችን

አምላክ ታምሩን ላሳየብህ

ጩኸት ድምፁህን የሰማልክ

በርጠሚዎስ ሆይ አትተወዉ

አዳኝ ጌታህን ተከተለው

እውርነቴን ያስቀረልኝ

ላይኖቼ ብርሀን የሰጠልኝ

ሁሌም ከእርሱ ጋር እኖራለው

አዳኜን ትቼ የት ኤዳለው

በርጠሚስዎስ ሆይ ታድለህል

የመዳን ፀጋ ተሰጥቶህል

እፁብ ድንቅ ነው የአምላክ ስራ

እውር የሆነው አይንክ በራ

ይህን ጌታዬን ምል ልበለው

ለውለታውስ ምን ልክፈለው

ስሙን ላወድስ ላመስግነው

የአምላክ ክፍያ ይህ ብቻ ነው

አስራ ሁለት አመት ደም ሲፈስሽ

አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር 

ሰዎች ሲንቁ ሲንቁሽ

ማን ፈወሰሽ አንቺ ሴት

ያበቃሽ ማን ነው ለድንት

እምነትሽ አድኖሻል አለኝ

አይል ወጣ ከርሱ የሚያዕናናኝ

የጌታ ልብሱን ብዳብሰው

ደሜም ቀጥ አለ ላወድሰው

በቤተ ሳይዳ ባልጋ ስትኖር

በመጠመቅያው በወንዙ ዳር

ደውይ ስትሆን በሽተኛ

እንዴት ተፈወስክ አውጋን ለኛ

አልጋ ታቅፌ ስንገላታ

መዳን ትሻለክ አለኝ ጌታ

አምላኬ እእርሱ ፈወሰኝ

አልጋህን ይዘህ ኺድ አለኝ

ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን

ኢትዮጵያንና ህዝቦቿን{፪}

ድንበር የሚጠብቁትን{፪}

ጠብቅ እግዚአብሔር ሠራዊቷን{፪}

የደም መፊት አትሁን ደም አይፍሰስባት

ካንተ የመነጨ ሰላም ይስፈንባት

አሸናፊ እንድትሆን ለስምህ ተገዝታ

አይንህን ሳትመልስ እያት ጠዋት ማታ

ሰንሰለት ሲፀና ለመከራ ፈርቶ

ኢትዮጲያዊ መልኩን አይቀይርም ከቶ

ድንቁን ብርሃን ያያል ወቶ ከጨለማ

በመንገዱ ሁሉ አዳኝ ቀኝ ቀድማ

እጅግ የፈተናት ተናቅሎላት መርዙ

ከእግሮቿ በታች ጠላቶች ይገዙ

ደጅ ስትጠና እጆቿን ዘርግታ

ጠብቅ ሠራዊቿን ዱሩ እንዳይፈታ

ከራሳቸው ይልቅ ኢትዮጵያን ወደዱ

ደም ከፍለው ሊያቆዮት በዱር ተሰደዱ

በሃሩር በውርጩ የሆኗትን አጥር

በማይፋቅ ቀለም ፃፍቸው ለክብር

የልቤን_ሁሉ

የልቤን ሁሉ ለማን ላማክር

እመቤቴ ሆይ ከአንቺ በቀር

የደካማው ሰው መጠጊያ እኮነሽ

ሃዘን ጭንቀቴን የምረሳብሽ

ቅዱሳን አበው አንቺን መረጡ (2)

ከሲኦል ዓለም ስላመለጡ

ፃድቅ በስራው ያኔ ሲድን(2)

እጠራሻለሁ ድንግል አንቺን

#አዝ

የጭንቄ ደራሽ አክኪሌ ነሽ(2)

ቂም በቀል አያውቅ የዋህ ልብሽ

ልቤ ለፍቅርሽ ሰፊ ስፍራ አለው (2)

በአዘ ንኩኝ ሠዓት እጠራሻለው

#አዝ

ዋሴ ነሽ ለእኔ ድንግል እናቴ(2)

ስምሽ ጠበቀኝ ከልጅነ ቴ

አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር 

ሁልጊዜ ለእኔ በጎ ያረግሽልኝ(2)

ምን ልበል ላንቺ ቃላትም የለኝ

#አዝ

ለአዘንኩኝ ለእኔ ደስታዬ ነሽ(2)

ያረጋጋሽኝ ፈጥነሽ ደርሰሽ

ስምሽ ሃጥአንን የሚቀድስ(2)

ከሞት ወደ ህይወት የሚመልስ

#አዝ

የመንገዴ ስንቅ የርሃቤ መርሻ(2)

ለታመመ ሰው ነሽ መፈወሻ

የተማጸነ በስምሽ አምኖ(2)

ማን አፍሮ ያውቃል አንቺን ለምኖ

አስታርቂኝ

አስታርቂኝ ድንግል ማርያም*

አስታርቂኝ ድንግል ማርያምጀ

ከልጅሽጀ ከመድሃኒዓለም

አዝ::::::

አስታርቂኝ ሀጢያትን ሰርቼ

" ጫካ ውስጥ ቆሜያለው

" ስራዬ አሳፍሮኝ

" ዘውትር አነባለው

" ልጄ ሆይ በሉ

" አምላኬ ሲጣራ

" እነሆኝ ለማለት

" አንደበቴ ፈራ

አዝ:::::

አስታርቂኝ ሁብቴን ተካፍዬ

" ከገዛ አባቴ

" ከቤተ ተሰደድኩ

" ይሻለኛል ብዬ

" ገፍቼ ወጥቼ

" የቤቴን እንጀራ

" ልበላ ተመኝው

" ከእንስሳት ገበታ

አዝ::::::

አስታርቂኝ ወደ አባቴ ልሂድ

" አሁን ተነስቼ

" ይቅርታ ልጠይቅ

" እግሩ ስር ወድቄ

" ልጅነቴ ቀርቶ

" አድርገኝ ባርያህ

" ከሞያተኞችክ

" እንዳንዱ አርገህ

አዝ:::::

አስታርቂኝ ገና እሩቅ ሳለው

" አባቴ አይቶኝ

" ወደኔ እሮጦ

" አቅፎ እየሳመኝ

" ጠፍቶ የነበርው

" ተገኘልኝ አለ

" ሞቶ የነበረው

" ደግሞም ህያው ሆነ

በበረሃው በሀሩሩ

በበረሃው በሀሩሩ

በሚያስፈራው በባህሩ

እስራኤልን የታደገው

በክንፎቹ የጋረደው ሚካኤል ነው





ሚካኤል ነው አፅናኝ ደጋፊዬ

"" በዱር በበረሃ

"" ነፍሴን ያረካልኝ

"" ከአለቱ ውሃ

የፊቴ ፈገግታ የውስጤ ፍስሐ

ከአምላክ የተሰጠኝ በረከት አምሐ

ሚካኤል ነው መብረቅ ያወረደው

"" ጠላት ድል የነሳው

"" የባህራን ወዳጅ

"" ሀዘኑን ያስረሳው

ቤቱን የሰራለት በእግሮቹ ያቆመው

እንደ እናት እንደ አባት ደግሶ የዳረው

ሚካኤል ነው ክሴን ያስቀደደ

"" የበደሌን እዳ

"" በአማላጅነቱ

"" ያዳነኝ ከፍዳ

በመንገዴ ሁሉ እኔን እየረዳ

ፍቅሩን ጽፎት አልፏል በልቤ ሰሌዳ

እልል_በሉ

እልል በሉ በአንድነት ዘምሩ

አመስግኑ ለክብሩም ዘምሩለት

እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም በሉ

በኃጢያት ባርነት ስንኖር ተገዝተን

ከቤቱ ስንርቅ ትእዛዙን አፍርሰን

አይቶ ዝም ላለን ጠላቶቹ ሳለን

ውለታው ግሩም ነው ክብር ለእርሱ ይሁን/2/

አዝ - - - - - - -

ራሱን አዋርዶ እኛን አከበረን

ሥጋውና ደሙን ብሉ ጠጡ አለን

መልካም እረኛ ነው የሚያሳጣን የለም

ምስጋና ይድረሰው ለመድኃኔዓለም/2/

አዝ - - - - - - - - -

ሕይወቱን የሠዋ እንደ አምላክ ማን አለ

ለሰው ልጆች ብሎ በመስቀል የዋለ

ፍቅሩም አይለካ አያልቅም ቢወራ

ከሰማያት ወርዶ ሆነ ከእኛ ጋር /2

አዝ - - - - - - - - - -

ሥራውን እናድንቅ እንዲህ ለወደደን

ከማያልቀው ፍቅሩ በረከት ላደለን

ለማይገረው ለአማላክ ስጦታ

ውዳሴን እናቅርብ እንዘምር በአልልታ

ኦ_ክርስቶስ

ኦ ክርስስ ኦ አምላክ ብሩህ ነህ/2/

ልቦናዬን አብራው በጥዑም ቃልህ/2/

አዝ

የታቦር ደመና =ክርስቶስ

የሲና ልምላሜ= ክርስቶስ

ምነው ሙሴን በሆንኩ=ክርስቶስ

እንዳይህ ቀድሜ = ክርስቶስ

የዮርዳኖስ ውሃ =ክርስቶስ

በላዬ ሲፈላ =ክርስቶስ

የሐንስን በሆንኩ እንዳይህ በተድላ

አዝ

ነበልባል ሐመልማል = ክርስቶስ

ተዋህዶ ሲና = ክርስቶስ

ሙሴ ከሩቅ ሆኖ= ክርስቶስ

አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር 

ተመልክቷልና =ክርስቶስ

በቀረበ ጌዜም =ክርስቶስ

ነገሩን ሲረዳ= ክርስቶስ

ለእሥራኤል ሾምከው ሁሉ እንዳይጎዳ

አዝ

ሙሴ በበትሩ = ክርስቶስ

ኤርትራን ሲመታ =ክርስቶስ

ተሻገሩ እሥራኤል =ክርስቶስ

በብዙ ደስታ =ክርስቶስ

ያልተደሰቱማ =ክርስቶስ

የፈርኦን ሠራዊት =ክርስቶስ

እየተሰጠሙ ቀሩ ወደ ጎላ

አዝ

ትንቢቱ ጸደቀ =ክርስቶስ

የኢሳይያስ= ክርስቶስ

ድንግልም ወለደች = ክርስቶስ

በመንፈስ ቅዱስ= ክርስቶስ

ምነው ባደረገኝ = ክርስቶስ

እንደ ሰሎሜ = ክርስቶስ

ጌታዬ ሲወለድ ለማመስገን ቆሜ

አዝ

ሐዋርያት ሁሉ =ክርስቶስ

ዞረው ያስተማሩት= ክርስቶስ

ወንጌልህ ብርሃን ነው = ክርስቶስ

የዓለም መድሃኒት = ክርስቶስ

ዮሐንስ እንዳለው = ክርስቶስ

ጥምቀት ለንሰሐ = ክርስቶስ

እጠመቀዋለሁ የጎንህን ውሃ

አዝ

ሚካኤል በቀኝህ = ክርስቶስ

ገብርኤል በግራ=ክርስቶስ

ቅውማን የሆኑት = ክርስቶስ

ሁሉም በየተራ = ክርስቶስ

ሱራፌል ኪሩቤል = ክርስቶስ

ዐይናቸው የበዛ = ክርስቶስ

ያመሰግኑሃል አንተን የዓለም ቤዛ

ገብረ ሕይወት ገብረ ሕይወት /፪/

ከንጉሳ መጣ ሊባርካት

ኢትዮጵያ መጣ ሊጠለልባት

ገብረ ሕይወት በዝቋላ ገዳም

ገብረ ሕይወት 100 ዓመት ጸለየ

ገብረ ሕይወት አባታችን ለእኛ

ገብረ ሕይወት ጌታን ተማጸነ

ገብረ ሕይወት በባህር ውስጥ ጠልቀህ

ገብረ ሕይወት ማርልኝ ብለሃል

ገብረ ሕይወት ለኢትዮጵያዊያን

ገብረ ሕይወት ምህረት ለምንሃል

ገብረ ሕይወት የእናትህን ጡት ሳትቀምስ

ገብረ ሕይወት የኖርክ በበረሀ

ገብረ ሕይወት ልብስህ ፀጉር ብቻ

ገብረ ሕይወት እጹብ የአምላክ ስራ

ገብረ ሕይወት እንማጸናለን

ገብረ ሕይወት ሁላችን በአንድነት

ገብረ ሕይወት ጸሎትህ እንዲያዋጣን





ገብረ ሕይወት ከሐጢአት ከመቅሰፍት

ሰው ሆይ ደስይበለን

ሰው ሆይ ደስ ይበለን በአምላካችን

ከሃጢአት ባርነት ነፃ ባወጣን

ተነሱ እናመስግን ውለታው ብዙ ነው

ምን ይከፈለዋል ተመስገን ብቻ ነው

በሃጢአት በሽታ ወድቄ ሳለሁኝ

መድሃኒት ከርስቶስ ከውድቀቴ አነሳኝ

ስጦታው ብዙ ነው ለእኔ የሰጠኝ

ተመስገን ብቻ ነው አምላክ ለአንተ ያለኝ

አዝ.....

እንደ በርጠሚዎስ ዕውር የነበርኩኝ

ዛሬ ግን በአምላኬ ደህንት አገኘሁኝ

ሕጉ ለመንገዴ ብርሃን ሆኖኛል

የእርሱ ስለሆንኩኝ ሰላሙም ሰጥቶኛል

አዝ.....

በድንቅ አጠራርህ በፍቅር የጠራኸኝ

ከአጋንንት እስራት ነፃ የወጣኸኝ

አልፋና ኦሜጋ ዘላለም የምትኖር

ኤልሻዳይ የሆንከው አማኑኤል ተመስገን

አዝ.....

የዕዳ ደብዳቤዬን ጌታዬ የቀደደው

የማዳንህን ሥራ በዓይኔ አይቻለሁ

ቸርነቱ አያልቅም ድንቅ የሆነ ጌታ

ስሙን እናወድስ እንዘምር በእልልታ

አዝ...

ሐዋርያውመነኩሴ

ሐዋርያው መነኩሴ የመረጡት ሥላሴ/2/

ተክለሃይማኖት ሆኗል ጠበቃ ለነፍሴ /2/

ዳሞት ይናገረው ያንተን ሐዋርያነት

የወንጌል ገበሬ የጣኦታት ጠላት

ጸሎተኛው ቅዱስ አባ ተክለሃይማኖት

ክንፍን የተሸለምክ እንደ ሰማይ መላእክት /2/

ብራናው ሲገለጽ ገድለ ተክለሃይናኖት

ከሰው ልጅ ልቡና ይወጣል አጋንንት

የቅዳሴው እጣን ሲወጣ ከዋሻው

ምድርን ይባርካል ጸሎቱ ምህላው/2/

ከሱራፌል ተርታ ቆመህ በማጠንህ

ሥሉስ ቅዱስ እያልህ ስታመሰግን

ጸሎት ትሩፋትህ ትጎትና ስግደትህ

ጾምህ ከፍ አድርጎ ሰማይ አደረሠህ/2/

ዛፉ ሲመነገል አምላክ የተባለው

ሞቶሎሚ ሲያፍር ትልቅ ሰው ነኝ ያለው

የጻድቁ ጸሎት ብዙ ነው ምስጢሩ

ስድስት ክንፉ አወጣ ቢቆረጥ አንድ እግሩ /2/

የኢትዮጵያን ምድር አረስከው በመስቀል

ጭንጫው ፈራረሰ ተዘራበት ወንጌል

ትናንት የዘራኸው ዛሬም ለእኛ ሆንዋል

አምላክ ተክለ አብ ብለን ተምረናል

ዮም_ፍስሐ_ኮነ

ዮም /ፍስሐ ኮነ/(፪)

በእንተ ልደታ ለማርያም

በባርነት ሳለን ● ፍስሐ ኮነ

አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር 

ኃጢአት በአለም ነግሳ ● ፍስሐ ኮነ

በድንግል መወለድ ● ፍስሐ ኮነ

ቀረልን አበሳ ● ፍስሐ ኮነ

እግዚአብሔር መረጠሽ ● ፍስሐ ኮነ

ልትሆኚው እናቱ ● ፍስሐ ኮነ

ይኸው ተፈፀመ ● ፍስሐ ኮነ

የዳዊት ትንቢቱ ● ፍስሐ ኮነ

የሔዋን ተስፋዋ ● ፍስሐ ኮነ

የአዳም ዘር ህይወት ● ፍስሐ ኮነ

የኢያቄም የሐና ● ፍስሐ ኮነ

ፍሬ በረከት ● ፍስሐ ኮነ

ምክንያተ ድኂን ● ፍስሐ ኮነ

ኪዳነምህረት ● ፍስሐ ኮነ

ድንግል ተወለደች ● ፍስሐ ኮነ

የጌታዬ እናት ● ፍስሐ ኮነ

በሔዋን ምክንያት ● ፍስሐ ኮነ

ያጣነውን ሰላም ● ፍስሐ ኮነ

ዛሬ አገኘነው ● ፍስሐ ኮነ

በድንግል ማርያም ● ፍስሐ ኮነ

የምስራች እንበል ● ፍስሐ ኮነ

ሀዘናችን ይጥፋ ● ፍስሐ ኮነ

ተወልዳለችና ● ፍስሐ ኮነ

የአለም ሁሉ ተስፋ ● ፍስሐ ኮነ

ጽኑ ሰማዕት የእምነት አርበኛ

አርሴማ ነይ ነይ ወደኛ

ነይ ነይ ቴድሮስ አትናስይ

>> >> በስዕለት ያገኙሽ

>> >> ብሉይን ከሀዲስ

>> >> ጠንቅቀሽ የተማርሽ

>> >> በፍፁም ትህትና

>> >> በጸሎት የተጋሽ

>> >> አርሴማ ልዩ ነሽ

>> >> አምላክ የመረጠሽ

ነይ ነይ ውበትም ሀሰት ነው

>> >> ደም ግባትም ከንቱ

>> >> ንብረት ትዳር ሁሉ

>> >> አላፊ ውዕቱ

>> >> ንግስት መባልን

>> >> በፍጹም ሳትሻ

>> >> አለምን በመናቅ

>> >> ገባች ወደዋሻ

ነይ ነይ አረመኔው ድርጣድስ

>> >> ቢያሰቃይሽም

>> >> ውበቴ ክርስቶስ

>> >> ነው ብለሽ ሰበክሽ

>> >> አንገትሽን ለሰይፍ

>> >> አሳልፈሽ ሰጠሽ

>> >> ክብርሽም ተገልጾ

>> >> ለአለም አበራሽ

ነይ ነይ አርአያ ልትሆኝን

>> >> ለእኛ ለሁላችን

>> >> ፈፅመሽ አሳየሽ

>> >> ታላቅ ተጋድሎሽን

>> >> ይህን አለም ድል መንሳት





›› ›› አቅቶናል እና

›› ›› አርሴማ አትለይን

›› ›› በእምነት እንድንጸና

ምን ሠማኽ ዮሐንስ

ምን ሠማኽ ዮሐንስ /በማሕጸን ሳለኽ/፪/

ሕጻን ሆነኽ ነብይ /ለክብር የተጠራኽ/፪/

እንደ እምቦሳ ጥጃ /ያዘለለ ደስታ/፪/

ምን ዓይነት ድምጽ ነው /ምን ዓይነት ሠላምታ/፪/

ከተፈጥሮ በላይ ያሰገደ ክብር

እንዴት ቢገባኽ ነው የአምላክ እናት ፍቅር

ሌላ ድምጽ አልሰማም ከእንግዲህ በኋላ

ለውጡኛልና የሰላምታ ቃሏ

በረሐ ያስገባኽ ለብዙ ዘመናት

ምን ያለ ራእይ እንዴት ያለ ብስራት

እንደ አዲስ ምስጋና ስልቱ የተዋበ

ተደምጦ የማያውቅ ቄራሽ ያልታሰበ

ከሴት ከተገኙ ከደቂቀ አዳም

ድንግል ሰለሆነ በሕይወቱ ፍጹም

በማሕጸን ሳለ ተመርጦ በጌታ

ለማዳመጥ በቃ የኪዳን ሠላምታ

ከተፈጥሮ በላይ ያሰገደ ክብር

እንዴት ቢገባኽ ነው የአምላክ እናት ፍቅር

ሌላ ድምጽ አልሰማም ከእንግዲህ በኋላ

ለውጡኛል የሠላምታ ቃሏ

ለማርያም

ለማርያም/4/

እንዘምራለን ለዘለዓለም/2/

የተዘጋች ደጅ.....ለዘለአለም

ሕዝቅኤል ብሏል.....ለዘለአለም

ንፅህት ናት በእውነት.....ለዘለአለም

በፍፁም ድንግል.....ለዘለአለም

አብነት አድርገን.....ለዘለአለም

እኛም እርሱን.....ለዘለአለም

በፍፅም ፍቅር እንዘምራለን/2/

የዋህት እርግብ..... ለዘለአለም

ሰላም አብሳሪ..... ለዘለአለም

ለጨለማ ሕይወቴ..... ለዘለአለም

ብርሃንን አብሪ..... ለዘለአለም

እማፀንሻለሁ..... ለዘለአለም

ድንግል ለነፍሴ..... ለዘለአለም

አደራ ቅድስት አንቺ ነሽ ዋሴ/2/

እጅግ የበዛ ነው..... ለዘለአለም

ያለኝ ፍቅር ..... ለዘለአለም

አይወሰንም..... ለዘለአለም

አይነገርም..... ለዘለአለም

በእርሷ ደስ ይለኛል..... ለዘለአለም

ሀሴት አደርጋለሁ..... ለዘለአለም

ስሟን እየጠራሁ እዘምራሁ/2/

ነፀ ነፀ ስላት..... ለዘለአለም

ቀንና ሌሊት..... ለዘለአለም

አትለየኝም ..... ለዘለአለም

ለእኔስ ቅርቤ ናት..... ለዘለአለም

እፁብ እፁብ ብለው..... ለዘለአለም

አመሰገኗት..... ለዘለአለም

ክብሯን ሊገልፁ ቢያጥራቸው ቃላት/2/

እንደ ሠማይ ከዋክብት ቢበዛልኝ ምን ነዋ ።

አማን በአማን አማኑኤል ተመስገን

አማን በአማን አማን በአማን

አማኑኤል ተመስገን

ለእዚህ ፍቅርኽ ምን ልክፈልህ /፪/

ቃናው ጠአፈጠኝ ውዳሴሽ

ቃናው ጠአፈጠኝ ውዳሴሽ

ቆሜ ስዘምር ለሥምሽ

/ማርያም ማርያም

ቤዛዊተ ኩሉ ዓለም/፪/

ድብቁን ኃጢአት አንተ ብትገልጸው

ያቅር ብለኽኝ ባትሸፋፍነው

እንደ ሰው በቀል ቢኖር ጌታ

ለኔ ኃጢአትስ የለውም ቦታ

ከማናቸው ውዳሴ ከ የቱ ተነስቼ

ምስጋናሽን ልጀምር እኔም እንደ አባቶቼ

የአምላክ እናት ምስጋናሽ እንደ ባሕር አሸዋ

እንደ ሠማይ ከዋክብት ቢበዛልኝ ምን ነዋ

በየደቂቃው ኃጢአት ስሰራ

ስሰርቅ ስበድል አንተን ሳልፈራ

አንተ ግን ፊትህ ምንም ቢቀየም

በቁጣህ በትር አልገረፍከኝም

ኤልሳቤጥ በሠላምታሽ በመንፈስ ስትሞላ

ምስጋናን አቀረበች መልዓኩን ተከትላ

የአምላክ እናት ምስጋናሽ እንደ ባሕር አሸዋ

እንደ ሠማይ ከዋክብት ቢበዛልኝ ምን ነዋ

ምሕረትህን ልከህ አድነኝ ዛሬ

ታክቶኛልና በኃጢአት መኖሬ

አለም በኃጢአት እየሳበችኝ

በጽድቅ ደስታ መኖር አቃተኝ

በ ብርሐኑ መስቀል ኤፍሬምን ብትባርኪው

ከፊትሽ ታጥቆ ቆመ ጀመረው ውዳሴሽን

የአምላክ እናት ምስጋናሽ እንደ ባሕር አሸዋ

እንደ ሠማይ ከዋክብት ቢበዛልኝ ምን ነዋ

የኃጢአት ጉዞ ጣፋጭ ቢመስልም

ውጤቱ መሮ ፍጹም አይጥምም

እንደ በደሌ ስላልከፈልከኝ

ተመስገን እንጂ ሌላ ምን አለኝ።

ከ ገብርኤል ሠላምታ ምስጋናሽን ተምሬ

ከ ፊትሽ አሸበሸብኩ እኔም በ አዲስ ዝማሬ

የአምላክ እናት ምስጋናሽ እንደ ባሕር አሸዋ

አንቺ የወይን ሀረግ

አንቺ የወይን ሀረግ ድንግል ልምላሜሽ የበዛ(2)

ምግብ ሆኖ(2)ተሠጠን ፍሬሽ ለኛ ቤዛ(2)

አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር 

ፊደል ትመሥያለሽ ድንግል ወንጌል ትወልጃለሽ(2)

ለመላእክት(2)የማይቻል ነበልባሉን የቻልሽ(2)

ባንቺ ሠማይነት ድንግል የወጣው ፀሀይ(2)

ብርሀን ነው(2)ለዓድቃን ሥሙም አዶናይ(2)

የመሶብ ምሳሌ ድንግል የኪነብ መገኛ(2)

በሥጋችን በነፍሳችን እንዳንራብ አንቺ አለሽን ለኛ(2)

አመጸኛው ልቤ ዛሬስ መች ይተኛል

በኃጢአት በዝሙት በስርቆት ይዋኛል

ወደ ቀድሞ ማብሩ እዳይመለስ

ፍቅርሕ በእኔ ሰርጾ ኃጢአቴን ደምስስ

በደላችንን ሁሉ ሳታስብ ትተህ

በምጽአት ሰዓት ከጻድቃን ቆጥረህ

ነጭ ልብስ ለብሰን ሆነን ከአንተ ጋራ

በሩ ሳይዘጋ አስገባን አደራ።

እግዚአብሔር ሆይ ርዳኝ

እግዚአብሔር ሆይ እርዳኝ ቸርነት አድርገህ /፪/

እድሜ ለንሰሃ እንደ ሕዝቅያስ ሰጥተህ /፪/

ጠማማውን ልቤን በቃልህ አቃንተህ

አላቀውም ብሎ ሲጠየቅ ያመጸው

ዶሮ እስኪጮህ ድረስ ሦስት ጊዜ የካደው

የጅረት ወንዝ ነው የሰጠኸው ዕንባ

ጴጥሮስ ተጸፅቶ ንስሐ እንዲገባ

ጽዋው እንዳይደርሰኝ የይሁዳ እድል

ልጅህ ሆኖ ውሎ ኋላ መከብለል

ጴጥሮስ እድለኛው አልቅሶ ተማረ

በትዕቢቱ ይሁዳ እንደወጣ ቀረ

ዘመኗን በሙሉ በዝሙት አቃጥላ

ለንሰሐ ጠራት ጌታ በገሊላ

ታድሳ ተነሳች በእንባዋ ብዛት

እግሩ ሥር ተደፍታ ማርያም መግደላዊት

መነነ

መነነ ተ/ሃይማኖት መነነ /2/

አሰረ ወንጌል ዴገነ

በእምነቱ ጸና ========== መነነ

ተጋድሎን ፈጸመ ======== መነነ

ተክልዬ በአንድ እግሩ =====መነነ

ሰባት ዘመን ቆመ ======= መነነ

የጽድቅ ስራን ሰራህ ======= መነነ

የእምነቱ ገበሬ /2/ ======= መነነ

ለእኛ አርአያ ሆኗል ======= መነነ

የዘራኸው ፍሬ ======== = መነነ

የኢትዮጵያ ብርሃን ======= መነነ

ተ/ሃይማኖት /2/ ======== መነነ

ሀገርክን አስባት ======== መነነ

ዛሬም አትተዋት ======== መነ

በተክልዬ ገዳም ======= መነነ

አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር 

ዲያቢሎስ ታሰረ======= መነነ

ለብዙ ዘመናት======== መነነ

በባርነት ኖረ ======= = መነነ

ድንጋይን ፈለጠ =======መነነ

እንጨትን ሰበረ ======= መነነ

እንዳይነቃነቅ ======== መነነ

በግዘት ታሰረ ======== መነነ

መነነ ገብረ ክርስቶስ መነነ /2/

አሰረ ወንጌል ይገነ

እናቱ ለሰርጉ ======== መነነ

ጃኖ አሰርታለት ======= መነነ

አባቱ ለጫጉላው ====== መነነ

ሸር ጉድ ሲልለት ====== መነነ

ከደመቀ ሰርጉ ======= መነነ

ከዚያ ተድላ ደስታ ====== መነነ

ጭሎ ተሰደደ. ======መነነ

ፍቅር ያዞት ከጌታ======መነነ

ከደላው ቤት ወጥቶ ====== መነነ

ተጠማ ተራበ /2/ ======= መነነ

ከደመቀ ጫጉላው ======= መነነ

ጫካውን ወደደ ======== መነነ

የአባቱን ርስት ======= መነነ

ንግስናውን ትቶ ====== መነነ

ሸፈተ መነነ ======= መነነ

ላይመለስ ከቶ ======= መነነ

መነነች ክርስቶስ ሰምራ መነነች /2/

አለም በእኔ ዘንድ ሙት ነው እያለች

ከሞቀ ትዳርዋ ======= መነነች

ጥላ ተሰደደች /2/ ====== መነነች

ስለ ጌታ ፍቅር ======== መነነች

ተጠማች ተራበች ====== መነነች

ለሳጥናኤል ምህረት ====== መነነች

የለመነ ማን ነው. ===== መነነች

ያንቺስ ቅድስና ======== መነነች

እናቴ ልዩ ነው ======== መነነች

አስራ ሁለት አመት ====== መነነች

በባህር የኖረች ======== መነነች

ስለጌታ ፍቅር ======== መነነች

እራሷንየሰዋች ======== መነነች

የሁላችን እናት ======== መነነች

ክርስቶስ ሰምራ ነች ====== መነነች

አምላክ ሰው ሆነ

አምላክ ሰው ሆነ ሰው አምላክ ሆነ (2)

በድንግል ማርያም ተከናወነ

የአብ ሙሽራ የወልድ እናቱ

የመንፈሥ ቅዱሥ ፀረሀ ቤቱ

በሠማይ ሆኖ አብ አፀናሽ

ወልድም ለራሱ ቤት አረገሽ

መንፈሥ ቅዱሥ ነው(2) የፀለለሽ

ይህ ድንቅ ሚሥጥር በሉ ግሩም

ምሥጋና አቅርቡ ለዘላለም

አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር 

በሥነ ፍጥረት ይታወቃል

የዓለም ፈጣሪ የእግዚአብሔር

ደስ ይበላቹ ደስ ይበለን በሉ እልል

ከሦስቱ አካል ወልድ አንዱ አካል

መጣ ወረደ በገባው ቃል

ተፀንሶ ሳለ ወልድም ከናቱ

አልተነጠለም ከሦስትነቱ

ታምራት አርጓል ድዊ ፈውሷልባምላክነቱ

በኤፍራታ ምድር

በኤፍራታ ምድር በቤተልሄም/2/

ጌታ ተወለደ ከድንግል ማርያም/2/

ብራናዊው ኮከብ ከሰማይ ዝቅ አለ/2/

ፍጥረትም ዘመረ ሀሌ ሉያ እያለ/2/

አዝ.....

መንጋውን በሌሊት ሲጠብቁ እረኞች

ከሰማይም ሰሙ ታላቅ የምስራች

በመላእክት ግርማ ምድር ስታበራ

የሚያስጨንቅ ነበር እጅግ የሚያስፈራ

አዝ.....

ድንገትም የሰማይ ሰራዊት ተገልጠው

ባንድነት ዘመሩ ከኖሎት ጋር ሆነው

ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ብለው

ሰላምን በምድር በጎ ፍቃድ ለሰው

አዝ.....

ቤተልሄም ሄደው ጌታን ተሳለሙ

ከእናቱ ጋራ ሆነው በግርግም አገኙት

የመላእክትን ዜማ እረኞች አወሩ

በልዩ ምስጋና አምላክን ሲያከብሩ

አዝ.....

በመዝሙር ቢሆን ፍስሐ ደስታ

በዳዊት ከተማ ተወለደ ጌታ

ህፃን ከእናቱ ጋር በግርግም ፈለጉት

እርሱ ነው ለሰዎች የድነት ምልክት

#አይሸሽግ_እጡነቱ

አይሸሽግ እውነቱ

ማርያም ብፅዕት ናት

ማርያም ቅድስት ናት

ከእግዚአብሔር ያልተላከ

አይችልም ሊያወድሳት

ገብርኤል ከከፍታ ከራማ ታላቅ ቤቱ

ገሊላ የተገኘው ወደ ማርያም እህቱ

ከእግዚአብሔር መላኩን ተረዳን በሚስጥር

ለስሟ ክብርን ሰጥቶ ሰምተነዋል ሲያበስር።

በዘካሪያስ ቤት አቀረብሽ ምስጋና

የባርያውን ውርደት ተመልክቷልና

ፍጥረት ብፅዕት ካለሽ ሆኖ ባንድ ቃል

ላንቺ ያልዘመረ እንዴት ትውልድ ይባል

ቢያከብርሽ ገብርኤል በታላቅ ትትና

ልዕልናሽ በልጦበት ከእርሱ ቅድስና

ከልቧ መንጭቶ መች ሆነ ማክበሩ

እግዚአብሔር ልኮት ነው ላንቺ መዘመሩ

አንዳች አይጎልብኝ አንችን አወድሼ

ዝማሬን ባበዛ ያለኝን ጨርሼ





እንኳን ለማርያም ለአዶናይ እናት

ምስጋናን ሰጥቷታል ለአቤኔያል ዳዊት

አማላጅ ነው

በፍጡራን እና ፈጣሪ መካከል

ድርሻ የተሰጠህ ሰውን ለማገልገል

ተራዳዩ መልአክ ጠበቂው የእስራኤል

የመልአክት አለቃ ስሙ ነው ሚካኤል

አማላጂ ነው ሚካኤል/2/ የአምላክ ባለሟል

ለነሙሴ ለህዝበ እስራኤል

ፈርኦን በእስራኤል ልቡ ተፀጽቶ

ሲከታተላቸው ጦሩን አስከትቶ

ይመራቸው ነበር ሚካኤል በፋና

ሌቱን በብርሀን ቀኑን በደመና

ከባህር ያወጣህ ፀጋ ዘአብን

ከአረመኔው ንጉስ እግዚአርያን

ከልለህ የሠወርክ በታላቅ ታምራት

እኛንም አድነን ከአስፈሪው ሀጥያት

በአፎሚያ ላይ ሲፎክር ጠላት

ፈጥነህ የደረስከው ሊቀ መላእክት

እኛም ስንጠራህ በዛሬዋ ዕለት

ፈጥነህ ድረስ እና ሁነን እረዳት

ሙሴ እንደታዘዘው አነሣ በትሩን

እጁንም ዘረጋ ገሰፀው ባሩን

እንደግንብ አቆመው ባህረ ኤርትራን

በደረቅ አለፉ እስራኤላዊያን

መልአኩ ሚካኤል አማላጃችን

እንለምንህለን እንድጠብቀን

ጌታ በፍርድ ቀን ፃድቃንን ሲጠራ

ዋስ ጠበቃ ሁነን ሚካኤል አደራ

ትምክህቴ መድኃኒቴ

ትምክህቴ መዳኃኒቴ አንቺው ነሽ/2/

እመብርሀን/4/ምርኩዛችን

አዝ-----

ሸክም የከበደኝ ደካማነኝ እኔ

እረዳትም የለኝ ከአንቺ በቀር ለእኔ

እመአምላክ ደግፊኝ ቁሚልኝ ከጎኔ

አዝ-----

የሀጢያትን ቋጥኝ በጀርባዬ አዝዬ

እቅበዘበዛለው ተገፎ ፀጋዬ

በአንቺ እማፀናለው ነፍሴን በእጅሽ ጥዬ

ምርኩዝ መሰላሌ ጥላ ከለላዬ

አዝ-----

ልዩ ነሽ እናቴ ማርያም ድንግል

ማን አዛኝ እንዳንቺ ግራ ቀኝ ቢባል

በአንቺ ላይ አረፈ ልቤ ተረጋጋ

የሕይወቴ ተስፋ በአንቺ ተዘረጋ

አዝ-----

ፊዕሞ አርቂልኝ የኔን ክፉ ሽታ

በሽቶሽ መዓዛ አድያኝ እርካታ

የኪሩቤል አክናፍ የነፍሴ ዋስትና

ነይነይ እመቤቴ ምርኩዜ ነሽና

አዝ-----

አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር 

በፍቅርሽ ምስጋና ዝም እንዳልል ድንግል

አደበቴን ፍችው ህሊናዬም ይቁሰል

የፍቅርሽ መዓዛ ይፍሰስ በህይወቴ

በእቅፍሽ አድርጊኝ እንደልጅነቴ

የያሬድ ውብ ዜማ

የያሬድ ውብ ዜማ ድንግል እመቤቴ

ስጦታዬ ነሽበምን አንደበቴ

እንዴትስ ባለ ቃል ማርያም ልበልሽ

አዝ.....

ምድርና ሰማዩ ታምርሽን ይንገሩ

ፍጥረታት በሙሉ ስለ አንቺ ይመስክሩ

ተንግሮ የማያልቅ ድንቅ ነው ሥራሽ

ድንግል ሆይ እናቴ አምሳያ የለሽ

አዝ-----

ማርያም ድንግል ረዳቴ

የምትደርሽልኝ ነይ ስልሽ በቄንቀቴ

ታምርሽንም በዓይኔ አይቻለሁ

ጸዮን ሆይ ስልሽ ድንግል ሆይ እጠግባለሁ

አዝ.....

የእግዚአብሔር ጥበቡ ባንቺ ተገለጠ

የአዳም ዘር በሙሉ ከሞት አመለጠ

የመዳን ምክንያት ማርያም አንቺ ነሽ

ለፍጥረቱ ሁሉ መሰላል የሆንሽ

አዝ-----

ነገ ባላውቅ እኔንም ቢያስፈራኝ

አንቺ ካለሽኝ በፍጹም አልወድቅም

በፊትሽ እንድቆም ለምስጋና

ማርያም ልበልሽ በትህትና

አዝ.....

ትውልዱ በሙሉ ለምስጋና ይቁም

በአንቺ ስለሆነ የቀረለት መርገም

አዳም ከነልጁ በሰማይ በምድር

ማርያም ማርያም ይበል ታምርሽን ይናገር

አዝ-----

ጨለማውም ከፊቴ ተገፈፈ

ማርያም በምልጃሽ ልቤ አረፈ

ከጎኔ ነይ ስልሽ እጽናናለሁ

እሳት ገደሉን ሁሉንም አልፈዋለሁ

የቤታቱ ኮከብ

የቤታቱ ኮከብ የልዳው አንበሳ

ሶስት ጊዜ ሞቶ ጊዮርጊስ ተነሳ/2/

አዝ.....

በተጋድሎ ጸና....ቅዱስ ጊዮርጊስ

በእውነት መሰከረ...ቅዱስ ጊዮርጊስ

ሀያሉ ጊዮርጊስ...ቅዱስ ጊዮርጊስ

በሰይፍ ተመተረ...ቅዱስ ጊዮርጊስ

የልዳው አንበሳ...ቅዱስ ጊዮርጊስ

ጠላት አይገዛህ...ቅዱስ ጊዮርጊስ

ሰይጣንን ተዋጋው...ቅዱስ ጊዮርጊስ

ጎልማሳው ስጋህ...ቅዱስ ጊዮርጊስ

አዝ.....

ድዳኖስ ተቆጣ....ቅዱስ ጊዮርጊስ

ፅናትህን አይቶ....ቅዱስ ጊዮርጊስ

ሊቀጣ ተነሳ....ቅዱስ ጊዮርጊስ

በትቢት ተሞልቶ....ቅዱስ ጊዮርጊስ

ባንተላይ ወገኑ....ቅዱስ ጊዮርጊስ

ሰባ ነገስታት.....ቅዱስ ጊዮርጊስ

ከምድረ ገፅ አንተን....ቅዱስ ጊዮርጊስ





ፍፁም ለማጥፋት....ቅዱስ ጊዮርጊስ

አዝ.....

በመበለቶ ቤት .....ቅዱስ ጊዮርጊስ

ጊዮርጊስ ታምር ሰራ....ቅዱስ ጊዮርጊስ

ምሶሶ አለምልሞ.....ቅዱስ ጊዮርጊስ

እውራን አበራ.....ቅዱስ ጊዮርጊስ

ሰባት አክሊላትን ....ቅዱስ ጊዮርጊስ

ጊዮርጊስ ተቀበለ....ቅዱስ ጊዮርጊስ

ስለ ጌታ ፍቅር .....ቅዱስ ጊዮርጊስ

ባደባባይ ዋለ....ቅዱስ ጊዮርጊስ

አዝ.....

ዝክርህን ዘክሮ....ቅዱስ ጊዮርጊስ

ስምህን የጠራ....ቅዱስ ጊዮርጊስ

በጎብስም በስጋ....ቅዱስ ጊዮርጊስ

የለበት መከራ....ቅዱስ ጊዮርጊስ

ድራገንን አጥፋ....ቅዱስ ጊዮርጊስ

አርቅልን ከሻ.....ቅዱስ ጊዮርጊስ

በገዘሙት በሀዋያት....ቅዱስ ጊዮርጊስ

ደርሶብናልና....ቅዱስ ጊዮርጊስ

መርሕ ዘገነት

መርሕ ዘገነት /4/

አንቺ ነሽ/2/ ኪዳንምረህት

ቅድስት አመቤቴ የጌታዬ እናት /2/

ሆንሽ የተመረጥሽ ንፅሕት ቅድስት

አንቺ ነሽ /2/ ኪዳንምረህት

የሲና ሐመልማል የሰው ልጅ ህይወት /2/

አንቺን የመረጠ ይክበር መለኮት

አንቺ ነሽ /2/ኪዳንምረህት

አብ እሳት ወልድ እሳት መንፈስቅዱስ እሳት/2/

እባክህ ክርስቶስ ይህችን ቀን ቀድሳት

አንቺ ነሽ /2/ ኪዳንምረህት

አዘክሪ ድንግል ለልጅሽ በእውነት/2/

በደህና እንዲያደርሰን ለመጪው ዓመት

አንቺ ነሽ /2/ኪዳንምረህት

ዝናውን ሰምቼ ፈለኩት

ዝናውን ሰምቼ ፈለኩት

ከሾላ ላይ ሆኜ አየሁት

ከአንተ ጋር ነኝ አለኝ መድኀኒቴ

ዛሬስ መዳን ሆነልኝ ለቤቴ

የረከሰው ቤቴን ጌታዬ ሳይንቀው

ጨለማውን ገፍ ብርሃን አደረገው

ለገናና ክብሩ ለእርሱ ተንበርክኬ

ዛሬ ተለወጠ ጎስቋላ ህይወቴ

አዝ

እንደምን ወደደኝ ምን አግኝቶ ከኔ

ህይወቴ ያደፈ ነው የገባውን ኩነኔ

አርኩ ግን ጎበኘኝ በማዳን አዋጁአ

ስሙን አተመብኝ አደረገኝ ልጁ

አዝ

የአብርሃም አምላክ የእስራኤል መና

የጠፋውን ሊፈልግ ሊያደን መጥቷልና

እኔም ጎበኘኝ በማዳኑ ጥሪ

ወሮታውን ከፈይ ነፍሴ ሆይ ዘምሪ


አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር


ወስኑ(2) ለያዕቆብ (2)

አዝ------

ያአምላክን ይመስላል ወስኑ

ድንግል ውበትሽ ወስኑ

ሁለንተናሽ ውብነው ወስኑ

ነውርም የለብሽ ወስኑ

ድንግል የዳዊት ልጅ ወስኑ

የአባትሽን ቤት እርሺ ወስኑ

በአለሙ ንጉስ ወስኑ

ታይቶል ውበትሽ ወስኑ

አዝ-------

ስደተኛው ያዕቆብ ወስኑ

በመንገድ ተኝቶ ወስኑ

እጅጉን ተዕናና ወስኑ

ድንግል አንቺን አይቶ ወስኑ

ለኔ ለኋጢያተኛው ወስኑ

መድሐኒቴ ነሽ ወስኑ

ከለላ ሁኝልኝ ወስኑ

ጠላቴ እንዲሸሽ ወስኑ

አዝ------

ከገደል አፋፍ ላይ ወስኑ

ጎስቁላ ሕይወቴ ወስኑ

ድልድይ ሁኝት አንቺ ወስኑ

አሻግሪያት እናቴ ወስኑ

ነፍሴን አሳሪፊያት ወስኑ

በምልጃሽ ቅጥር ወስኑ

ቃልኪዳንሽ ከቧት ወስኑ

ዘላለም ትኑር ወስኑ

ተክለሃይማኖት ፀሀይ የኢትዮጵያ ሲሳይ

ተክለሃይማኖት ፀሀይ የኢትዮጵያ ሲሳይ

ምእራፈ ቅዱሳን/2/በነፍስም በስጋ አትለየኝ

የቅዱሳን አርእስት የዋሻው ብርሃን

የጸሎት ባለቤት የነዲያን መድኅን

ገና ስትወለድ አምላክ የመረጠህ

የድውያን እምነት ፈዋሹ አንተነህ/2/

አዝ .....

ገና በሦስት ቀን በሕፃንነትህ

ጌታን አወደሰው ቅዱስ አንደበትህ

ደግሞም እግዚአብሔር አስቦሃልና

በወጣትነትህ ወጣህ ለምነና/2/

አዝ.....

ሴትና ቀን ሳትመርጥ ከረምትና በጋ

ስትፀልይ ውለህ ስትጸልይ ነጋ

በመቀምህ ብዛት አንድ እግርህ ሲነሣ

ጸሎትህን ፈፀምክ ለስጋ ሳትሣሣ/2/

አዝ.....

ምነኛ ድንቅ ነው ቅዱስ የአንተ ብርታት

7 ዓመት ሙሉ በአንድ እግርህ ጸሌት

የአለም ግሳንግሷ ሀብቷ ሳያስብህ

ለኢትዮጵያ ጸለይክ ቆመህ በአንድ እግርህ/2/

አዝ.....

የሀይማኖት ተክል የኢትዮጵያ አባት

ምህረት ከአምላክ ለሀገርህ አሰጣት

እኛንም አግዘብ ጽድቅን እንድንሠራ

በተሰጠህ ስልጣን ጠብቀን አደራ/2.

አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር 

እግዚአብሔር የወደቁትን

ያነሳል የተረሱት ያስታውሳል

የተናቁት ያከብራል

አንተ በክብር ላይ ክብር ስጨምር

እረኛው ይሻማል በንጉስ ወንበር

ጌታ ትውዳለ የተናቁትን አንተ

ልብን እንጂ አታይም ፊትን

#አዝ

ሳሙኤል ልከ ጠርተ ትቀባለክ

ያንበሶቹን አፍ አንተ ትዘጋለክ

በጌርጌሲኖር በመቃብር ስፍራ

አየሁ አምላኬ ለሰው ልጅ ስትራራ

#አዝ

ጠላታችን ደርሳ ቢያስጨንቀንም

ትሞታለ ብሎ ቢዝትብንም

በሃሰት ቢጥለን ከመከራ ቤት

በእግዚአብሔር ቸርነት ወጣን ከስራት

#አዝ

ይደግፋል ክንድህ የተጋቁትን

ከሰው በታች ሆኑ የሚኖሩትን

ደስታ ትሰጣል ሃዘን አርቀህ

አይቀርም አልቅሶ አንተን ያመነህ

#አዝ

ጠላታችን ደርሳ ቢያስጨንቀንም

ትሞታለ ብሎ ቢዝትብንም

በሃሰት ቢጥለን ከመከራ ቤት

በእግዚአብሔር ቸርነት ወጣን ከስራት

ውለታዋ አለብኝ

ውለታዋ አለብኝ የዓድቃኔ ማርያም

ያንን ድንቅ ፀበል ታምሯን አረሳም

ስዘምርላት ሰቀኝ እኖራለው

የናቴን ደግነት ክብራን እገልፃለው

ዝናዋን ከሩቅ በመስማቴ

ወደሷ ብሄድ ወደ እናቴ

በደለኛ ነህ ሳትለኝ

እንዳዕናናችኝ ትዝ አለኝ

ከአይምሮዬ ከውስጤ አይጠፉም ታምሯ

ያረገችልኝ ሳለቅስ ቆሜ ከበሯ

እምነቷን ፊቴን ተቀብቼ

ፈዋሽ ፀበላንም ጠጥቼ

ይሄው ለመዳን በቅቻለው

ያንን መከራ አልፈለው

ከደጇ ሄዶ ኧረ ማን አለ ያፈረ

በጌታዬ እናት በዓድቃኔ የታመነ

የሰላም ደጇን በመርገጤ

ተመለሰልኝ ጤንነቴ

የሷስ ልዮ ነው ታምራቷ

ቢነገር አያልቅ ደግነቷ

እኔስ ገረመኝ የእመቤቴ ውለታ

ፍቅሯን እያሰብኩ እዘምራለው በልልታ

ባልጋ ቁራኛ የተያዙ

ደጇ ተቀምጠው ተፈወሱ

ታምሯን ቆመው መሰከሩ

ጧፋን አበሩ ሊዘምሩ

የኛ እመቤት የምንዱባን በረከት

ብለው ተቀኙ አከበሯት ባንድነት

ምግባረ ተክለአብ

በቃልኪዳንሽ አምኖ ለሠጠሽ ፈጣሪ

በምግባረ ሠናይ ነፍሴ ተጣጣሪ/2/

አዝ-----

በስመ አብ ወወድ ወመንፈስ ቅዱስ

ምግባረ ተክለአብ ብእሲ ሞገስ/2/

ይነገር ይሰማ እስካጥናፍ ድረስ

የሚሆንነው እና የህሙማን ፈውስ/2

አዝ-----

ጋሻና ጦር ይዞ ለማደን አራዊት

የሰውን ልጅን ሊያድን ሥላሴ መረጡት /2/

አጋዕዝተ አለም ፀጋን የሚሰጡ

ተክለሀይማኖት ብለው ስሙንም ለወጡ/2/

አዝ-----

በኪነተ እግሩ ኢትዮጵያን ቀድሶ

ወጣ ደብረ አስቦ ብፍጥነት ገስግሶ/2/

እግሩ እንኳን ቢቆረጥ በመቀም ብዛት

ለ 7 አመታት ፀና በፀሎት/2/

እውነት ነው

እውነት ነው አዎ እውነት ነው

መንገድ ነው አዎ መንገድ ነው

ህይወት ነው በእርግጥ ህይወት ነው

ኢየሱስ የጌቶች ጌታ ነው

ወደ እግዚአብሔር አብ የምንደርስበት

አንድያ ልጁን የምናምንበት

የህይወት መንገድ እርሱ ብቻ ነው

የባህሪ አምላክ ብለን ስናምነው

እውነት ነው አዎ እውነት ነው

ህይወት ነው በእርግጥ ህይወት ነው

መንገድ ነው አዎ መንገድ ነው

ኢየሱስ የአማልክት አምላክ ነው

በማርያም ስጋ የተገለጠው

ወልድን ስናውቅ ነው አብን ያወቅው

አብ በእርሱ እንዳለ እርሱም በአብ አለ

በሀይል በስልጣን የተካከለ

እውነት ነው አዎ እውነት ነው

መንገድ ነው አዎ መንገድ ነው

ህይወት ነው አዎ ህይወት ነው

ኢየሱስ እርሱ ጌታ ነው

ስጋውን ቆርሶ ደሙን አፍሶ

ህይወት የሰጠን በደልን ክሶ

እኛም ዳሰስነው በላን ጠጣነው

በዝግ ቤት ሳለን ገብቶ ያየነው

እውነት ነው አዎ እውነት ነው

ህይወት ነው በእርግጥ ህይወት ነው

መንገድ ነው አዎ መንገድ ነው

ኢየሱስ የጌቶች ጌታ ነው

ፈቅዶ ቢወሰን በአጭር ቁመት

ረቂቁ ቢገዝፍ በጠባብ ደረት

መንሹ በእጁ ነው ሁሉን ያጠራል

በአለም ሊፈርድ ዳግም ይመጣል

የአለም ቤዛ


አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር


የአለም ቤዛ መድሃኒአለም ነው
በመስቀል የተሰቀለው
ቀድሞ የነበረ መድሃኒአለም
ከአባቱ ጋራ መድሃኒአለም
ሁሉን የፈጠረ መድሃኒአለም
ሁሉንም የሠራ መድሃኒአለም
ስጋችንን ሊለብስ መድሃኒአለም
መጣ ከሰማይ መድሃኒአለም
ሞታችንን ሞተ መድሃኒአለም
ሲኦል እንዳናይ መድሃኒአለም

ድንግል ማርያም የጌታ አናት
ሞገሴ አክሊሌ ናት

በሄድኩበት ሁሉ ድንግል ማርያም
መንገዴን አቅንታ ድንግል ማርያም
ኑሮዬን አስተካክላ ድንግል ማርያም
በበረከት ሞልታ ድንግል ማርያም
የራሴ ላይ አክሊል ድንግል ማርያም
እንዳይወድቅብኝ ድንግል ማርያም
ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም
ጎኔ ቁሚልኝ ድንግል ማርያም

ተክለሃይማኖት አባታችን
መመኪያ ጥላ ጋሻችን
በቅዱስ ወንጌሉ ተክለሃይማኖት
ጣኦት የሰበረ ተክለሃይማኖት
በሰዎች ልቦና ተክለሃይማኖት
እምነትን ያኖረ ተክለሃይማኖት
ለእኛ የተሰጠ ተክለሃይማኖት
ከእግዚአብሄር ተክለሃይማኖት
ተክለሃይማኖት ነው ተክለሃይማኖት
ሰባኪ ወንጌል ተክለሃይማኖት

ሀብተማርያም ስንልህ
አድነን አውጣን ፈጥነህ
መከራና ችግር ሀብተማርያም
ሲበዛ ፈተና ሀብተማርያም
ለሰዎች ከብጇ ሀብተማርያም
ስኖር ያለ ምግባር ሀብተማርያም
ስዕሉ ፊት ቆሜ ሀብተማርያም
ስሜን አከበረ ሀብተማርያም
በሀብተማርያም ሀብተማርያም
ታሪክ ተቀየረ ሀብተማርያም

ሀብተማርያም ስንልህ
አድነን አውጣን ፈጥነህ

እግዚአብሔር እኛን ይወደናል
እግዚአብሄር እኛን ይወደናል
መላዕክቱን ለኛ ልኮልናል
'እንዲረዱን እንዲጠብቁን
መላእክቱ እንዲታደጉን/2/

መንገደኛ መስሎ መላኩ ሲራራ
በአሞት መስሎ በዚያ በተራራ
"የጦቢትን አይኑን ያበራ
ሩፋኤል ነው ለኛ ሚራራ/2/

ጣቢያና ጣቢት ይናገሩ

የመላኩን ታምር ይመስክሩ

"ይናገሩ ይገለጥ ክብሩ

የታወሩ ኡሉ እንዲበሩ/2/

ወለተ ራጉኤል ተናገሪ

የጫጉላ ቤትሽን ታሪክ አውሪ

``ተናገሪ ለህዝብ አብስሪ

ታምራቱን ምንም ሳትፈሪ /2/

ስባቱ ባሎችሽ መሞታቸው

የሚያሳዝን ነበር ታሪካቸው

``ሩፋዔልም ደረስልሽ

ጎጆሽንም ባረከልሽ /2/

እንግዲ ተደስች እልል በዪ

አስማንዲዮስ ወቶል ከአንቺ ላይ

``ህይወትሽን ሩፋኤል ዋጀው

ስላምሽን ለዓለም አወጀው/2/

ጣቢያ ይናገር በተራው

ያደረገላትን አለኝታው

"ወዲያው ደግሞ አባት ሆነው

ሽማግሌ ሆኖ ዳረው/2/

እኔም ልናገር በተራዬ

ያደረገልኝን አለኝታዬ

"ህይወቴን ሁሉ ለውጦታል

ልቦናዬን ፍቅሩ ማርኮታል/2/

እኔም ልናገረው በተራዬ

ቀሎልኛልና መከራዬ

"ሩፋዔል ነው እናት አባቴ

እለዋለው የስግይ ቤቴ/2/

በምን በምን

በምን በምን እንመስላት ድንግል ማርያምን

ምሳሌ የላትም የላተም ክብርዋን የሚመጥን/2/

የሙሴ ፅላት ነሽ የምህረት ቃል ኪዳን

የያእቆብ መሰላል የአብርሀም ድንኳን

የብርሀን መውጫ የኖህ ድንቅ መርከብ

የመላክት እህት "የእሩሀሩህን እርግ/2/

የሰለሞን አክሊል የአሮን በትር

የእዝራ መሰንቆ የጌዲዮን ፀመር

ድንግል እናቴ ናት የግድቃኖች በር

ሆና የተገኘች "የአምላክ ማህደር/2/

የቅዱሳን እናት የአርያም ንግስት

ስለተሸከመች መለኮተ እሳት

በስጋችን ፍቃድ ወድቀን እንዳንጠፋ

አማልዳ ታስተምረን "ከዚህ አለም ጣጣ/2/

ከማር ይጣፍጣል የድንግል መዐዛ

አምላክን አቅፍለች በሁለት እጅዋ ይዛ

አለሙ የዳነው በልጅሽ ነውና

እናታችን ዒኦን ይድረስሽ ምስጋና/2/

አባ አባ ፍቅርህ ይፅናልኝ

አባ አባ ነፍሮ ውሃ ጠጥቼ

አባ አባ ታምር አይቻለሁ

አባ አባ እባብ ና ጊንጡን

አባ አባ ተረማምጀለው

ተክለሐማኖት አቡዬ

አባ አባ ተክለሐይማኖት አቡዬ/2

በለኒ በለኒ ወልድዬ/2

አባ አባ እንኳን ሰው ምድራቱን

አባ አባ ጦም አያሳድርም

አባ አባ አምላክ ተክልዬ

አባ አባ ብዬ አፍሬ አላውቅም

አባ አባ ምድራዊ መልአክ ነህ

አባ አባ የህቲሳ አንበሳ

አባ አባ ለደብረ ሊባኖስ

አባ አባ አንተ ነህ ሞገሷ

አባ አባ ስማኒብያለው

አባ አባ ሳለህ በሰማይ

አባ አባ ከኪሩቤል ተርታ

አባ አባ ሆነህ ስትታዬኝ

አባ አባ ስምህም ሲጠራ

አባ አባ ገድልህ ሲነገር

አባ አባ አፀብ ድንቅን ያሰኛል

አባ አባ የተሠጠህ ክብር

አባ አባ አባቴ እልሃለው

አባ አባ ልጄ ሆይ በለኝ

አባ አባ የአባት ና የልጅ

አባ አባ እለት በእለት ሄጄ

አባ አባ ደጅ ስጠናው

አባ አባ ይሰማል ተክልዬ

አባ አባ ዛሬም ህያው ነው

አባ አባ እንቆሽቅል ፈትቶ

አባ አባ ደስ አሰኝቶኛል

አባ አባ የተክለሐይማኖት

አባ አባ ቡራኬው ደርሶኛል

ደስ ይበለን

ደስ ይበለን ደስ ይበለን

አምላክ አለ መሃላችን

ምን እንክፈል ለዚህ ስራህ

ገናና ነው አምላክ ክብርህ /፪/

ምሕረቱን አይተናልና

አድርሶናል አምላክ በጤና

ይችን ዕድሜ የጨመረልን

ለንስኃ ጊዜ የሰጠን

ኃጢአትህን ይታገስሃል

በቸርነት አምላክ ያይሃል

ደስታ ነው በሰማያት

በአንድ ኃጥአ የዕድቅ ሕይወት

አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር 

እልል በሉ የንበሻችሁ

በምሕረት ዓይኑ ያያችሁ

በችግር ቀን ያሰበን ሁሉ

አመስግኑ ዝምም አትበሉ

ድንግል ማርያም ትፀልያለች

ኃጥኡን ሰው ማረው እያለች

በድንግል ክብር እንኖራለን

በጽኑ ፍቅር አንድ እንዲያደርገን

ውዳሴ_ማርያም

ውዳሴ ማርያም እጮሃለሁ

ድንግል እናቴን እጣራለሁ

እንደ አባ ኤፍሬም ነፀ ባርኪኝ

ወድሰኒ ልጇ በፀኝ

ውዳሴ ማርያም በሠርግ ጸሎት ላይ

ውዳሴ ማርያም ዜማ ስናደርስ

ውዳሴ ማርያም ድንግል ትመጣለች

ውዳሴ ማርያም በቤተ መቅደስ

ውዳሴ ማርያም የብርሃን ምንጣፍ

ውዳሴ ማርያም ከፊቷ ተነጥፏል

ውዳሴ ማርያም ቅዱስ ኤፍሬም ታጥቆ

ውዳሴ ማርያም ያመሰግናታል

ውዳሴ ማርያም አባ ሕርያቆስም

ውዳሴ ማርያም ምስጋና ያደርሳል

ውዳሴ ማርያም የቅዳሴው ዜማ

ውዳሴ ማርያም ልብን ይመስጣል

ውዳሴ ማርያም በጎ ነገር ልቤ

ውዳሴ ማርያም አወጣ እያለ

ውዳሴ ማርያም ዳዊት በገናውን እየደረደረ

ውዳሴ ማርያም ለንጽሕናችን

ውዳሴ ማርያም መሠረት ነሽና

ውዳሴ ማርያም አንቺን ለማመስገን

ውዳሴ ማርያም ልቦናዬ ይብራ

ውዳሴ ማርያም ተፈሥሒ ድንግል

ውዳሴ ማርያም ኦ ቤተልሔም

ውዳሴ ማርያም ካንቺ ተወለደ

ውዳሴ ማርያም መድኃኔዓለም

ውዳሴ ማርያም ቅዱሳኑ ሁሉ

ውዳሴ ማርያም ዙሪያሽን ከበዋል

ውዳሴ ማርያም አባ ጊዮርጊስም

ውዳሴ ማርያም ንዒ ድንግል ይላል

ውዳሴ ማርያም በወርቅ ዙፋን ላይ

ውዳሴ ማርያም ተቀምጠሽ ሳይሽ

ውዳሴ ማርያም ልቤ ተሰወረ

ውዳሴ ማርያም ድንግል በግርማሽ

ዘምር_ዘምር_አለኝ

ዘምር ዘምር አለኝ ልቤ ተነሳሳ /2/

የአምላኬን ቸርነት እንዴት ብዬ ልርሳ

ያደረገልኝን እንዴት ብዬ ልርሳ

የሚቃጠለው ስም በፊትህ ምንድን ነው

ሰማይ እና ምድር ሁሉም ገንዘብህ ነው

ያለኝን ሰብስቤ ባሆረው በፊትህ

ዋጋ አይሆንም ጌታ ስለቸርነትህ

አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር 

ይበዛል ይሰፋል የእግዚአብሄር ምስጋና

አይቆምም በዘመን ማዕበል ነው እና

እንኳን ድንጋይ ቀርቶ ጣርያው ቢናድብን

የከንፈሬን ፍሬ ማንም አይወስድብኝ

የጳውሎስ የሲናስ መከራው ቢፀና

አልተውም ቅኔውን የአምላኬን ምስጋና

ሊያስጥለኝ አይችልም እስር ሰንሰለቱ

አለብኝ ውለታ የሰማይ አባቴ

የተደረገለት ብዙ የተቀበለ

ይኖራል በፍቅሩ እየተቃጠለ

ክብሬን ሁሉ ትቼ ልዘምርልህ

ይህ ነው ችሎታዬ ላንተ የምሰጥህ

ኢያራየኒ

ኢያራየኒ ዓይነ ሞት

ወይከበኒ ኩነኔ

ነፍሴን አደራ በሰማይ(፪)

ተክልዬ ፀሐይ

ጽላልሽዞረሬ ነይ መስክሪ

የተክለሃይማኖትን ገዳና አውሪ

የቁርቁሪት ፀበል ማር ወተት

ሁሉም ተፈወሱ ሲጠጡት(፪)

ትህትናህ ግሩም ነው ቅድስናህ

ሃይቅ እስጢፋኖስ አገልግለህ

ደብረ ዳሞ ዘልቀህ ክንፍ አወጣህ

ደብረ ሊባኖስ ላይ ፍፁም ፀናህ

ደብረ ሊባኖስ ላይ አርፏል አጽምህ

ከተታና ዳሞት ተሻግረህ

ባርያንን ሁሉ አማፈርክ

በንብ ቀፎ አርገው ቢጥሉህ

ሚካኤል በክንፉአቀፈህ(፪)

በደብረ አስቦ ውስጥ ጦር ተከለህ

ሃያ ዘጠኝ ዓመት ተጋድለህ

ወገዘህ ያረፈበት ነጠብጣቡ

ድውይ ይፈውሳል ቃልኪዳኑ(፪)

ይህን ሁሉ ፀጋ ተችሮሃል

ቁጥርህ ከመላዕክት ተስተካክሏል

አባቴ አባቴ ስልህ

ነፍሴን ታደገልኝ በምልጃህ(፪)

ብዙ ልጆች አሉት

ብዙ ልጆች አሉት ለስሙ ምስክር

በዙሪያው ያሉትን አብቅቷል ለክብር

ስለፍፁም ምልጃው ለኔማን ይለያል

መላኩ ሚካኤል ስለው ደስ ይለኛል

አዝ.....

ከመላዕክት ክብሩ ከፍ ከፍ ብሎ

በአምላኬ ተሾመ ዘንዶውንም ጥሎ

አሳዳጊዬነው ሆኖ እናት አባቴ

ሚካኤል ባለበት ይሸሻል ጠላቴ

አዝ.....

ከሚታየው ሁሉ ልቤ ከሚፈራው

አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር 

ካላየሁት ነገር ጠላት ከሰወረው

ያድነኛል ፈጥኖ በመንገዴ ወቶ

ሚካኤል ሀያሉ ከንፎቹን ዘርግቶ

አዝ.....

በባህራን ታሪክ በነተላፊኖስ

በአፎምያ መትረፍ በነ ዱራታኦስ

በነብዩ ዳንኤል መቸ ይፈጸምና

የሚካኤል ስራ ይቀጥላል ገና

አዝ.....

በጉዞ የረዳቹ በባህር በየብሱ

ፈጥኖ ደርሶላቹ እንባን ስታፈሱ

ስለታችሁ ሰምሯል ቁሙ ለዝማሬ

በሚካኤል ምልጃ የቆማችሁ ዛሬ

አዝ.....

ክብር ለሚገባው ክብርን እንሰጣለን

ንጉሥ ለወደደው እንሰግድለታለን

እንኳን ለሚካኤል ለሚቆም ጌታ ፊት

ክብርን እንሰጥ የለ ለምድር ሹማምንት

ሠዳዴ ሳጥናኤል - - - ቅዱስ ሚካኤል

ሊቀ መላእክት - - - - ቅዱስ ሚካኤል

እኛንም አድነን - - - - ቅዱስ ሚካኤል

ከሲኦል እሳት - - - - - ቅዱስ ሚካኤል

አዝ = = = = =

ከሊቀ ነብያት - - - - ቅዱስ ሚካኤል

ከነሙሴ ጋራ - - - - - ቅዱስ ሚካኤል

ሕዘበ እሥራኤልን - - - ቅዱስ ሚካኤል

ሚካኤል ሲመራ - - - ቅዱስ ሚካኤል

ቀን ደመና ጥሎ - - - ቅዱስ ሚካኤል

ሌሊት እያበራ - - - - - ቅዱስ ሚካኤል

ተሻገሩ ኤርትራን - - - -ቅዱስ ሚካኤል

ሁሉም በየተራ - - - - ቅዱስ ሚካኤል

ሀያል

ሀያል ሀያል ×4

ሰዳዲ ሳጥናኤል ×2

ሀያል ገባሪ ሀያል

ባሕራንኒ ይቤ

ባሕራንኒ ይቤ ኦ ዘነገደ ባህር /፪/

ርዒከዎ ለሚካኤል ወሰዕንኩ ጠይቆቱ ዘይብል/፪/

ባህራንኒ ይቤ /፯/

የሞቱን ደብዳቤ - - - ቅዱስ ሚካኤል

ሚካኤል አጥፍቶ - - - ቅዱስ ሚካኤል

ባሕራንን አዳነው - - - ቅዱስ ሚካኤል

በሠርግ ተክቶ - - - - ቅዱስ ሚካኤል

ባህራንን የረዳኸው

ተላፊኖስን ያዳነው

መላኩ ሚካኤል ነው ×2

የሞቱን ደብዳቤ የለወጠው

ከዕደ እረበናት ×4

ሶስናን ያዳናት ×2

ሚካኤል መልአከ ምህረት

አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር 

ዳቢሎስን ያዋረድከው

በእሳት ሰይፍ የቀጣኸው ×2

ሚዛንህ ትክክል ነው ×2

ሚካኤል ክብርህ ድንቅ ነው

በሀዘን በትካዜ ያየሁትን ብላቴና ×2

አፅናኝ አረጋጋኝ ×2

ማካኤል ሊቀ ደብረ ሲና

ሚካኤል ነው እሩህ መልአክ

ሚካኤል ነው እሩሩ መላክ

ሚካኤል ነው አዛኙ መላክ

የሚያፅናናኝ /2/

ፈጥኖ የሚረዳኝ

አዝ.....

ሚካኤል ነው በመጠመቂያዬ

ሚካኤል ነው በፀሎቴ ስፍራ

ሚካኤል ነው ሊረዳኝ የመጣው

ሚካኤል ነው ከእዮር ከራማ

ሚካኤል ነው ሀያሉ ሚካኤል

ሚካኤል ነው ሆነ ከኛ ጋራ

አዝ.....

ሚካኤል ነው የሚጠብቀኝን

ሚካኤል ነው በመንገዴ ሁሉ

ሚካኤል ነው የሚያሳድዱኝ

ሚካኤል ነው በሱ ይወድቃሉ

ሚካኤል ነው ለክብሩ መግለጫ

ሚካኤል ነው እልል እልል በሉ

አዝ.....

ሚካኤል ነው የእግዚአብሔር መላክ

ሚካኤል ነው ይረዳኛልና

ሚካኤል ነው ከፊት ከጎላዬ

ሚካኤል ነው እሱ ቆሞልና

ሚካኤል ነው ነብሴ ደስ ይበልሽ

ሚካኤል ነው አቅርቢ ምስጋና

የስሙ_ትርጓሜ

የስሙ ትርጓሜ ማን እንደ እግዚአብሔር ነው

የሰውን ወደ አምላክ የአምላክን ወደ ሰው

እኛን የሚረዳን ዘወትር በምልጃው

የመላዕክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ነው

ከጉድጓድ ተጥሎ ፍፁም ከሚያስፈራው

ከተራቡ አናብስት ዳንኤልን ያዳንከው

እኛንም ተራዳን ቸል አትበለን

ሰይጣን በተንኮሉ ወጥመድ ሳይጥለን

#አዝ

የከፋ ሰው ስራው ክፉ ሃሳብ ነውና

በቅንነት መንገድ ከቶ አይሄድምና

የሞቱን ደብዳቤ ለባህራን ሲሰጠው

ሚካኤል አጥፍቶ በደስታ ለወጠው

#አዝ

ገና ብላቴና ሳለው አንድ ፍሬ

ሰው ሁሉ ሲንቀኝ ምስጋናን ጀምሬ

ጸጋዬን አብዝቶ ያበቃኝ ለዚህ ክብር

የሚካኤል አምላክ ይመስገን እግዚአብሔር

ገና እንዘምራለን

ገና እንዘምራለን ገና እንዘምራለን

ገና እንዘምራለን ገና እንዘምራለን





እንደ መላዕክቱ ብርሃንን ለብሰን

ገና እንዘምራለን

ወላዲተ አምላክን ከፊት አስቀድመን

በዳዊት በገና መሰንቆ ታጅበን

ለሥላሴ ክብር ገና እንዘምራለን

ገና እንዘምራለን

በምስጋና ሰርዐት ከሰለጠኑት ጋር

ልብን የሚያስደስት መዝሙር እየዘመርን

ያልተሰማ ዜማ ያልታየ ምስጋና

ይፈልቃል አይቀርም ከእኛ ልቦና

ገና እንዘምራለን

በትዕቢት ሳይሆን በታላቅ ትህትና

በልዩ ተመስጦ በፍቅር ልቦና

ስራችን ይሆናል ለአምላክ ምስጋና

ገና እንዘምራለን

ዳዊት በተመጦ እርቃኑን ቢሆንም

ሜልኮን በዝማሬው ብትሰቅበትም

አምላክ ከፈቀደ እንዲያመሠግነው

በደስታ እንዳይዘምር ከልካዩ ሠው ማነው?

ገና እንዘምራለን

ደስ ይበልሽ

ደስይበልሽ/2/ ማርያም ንፅህይት ድንግል/2/

ደስይበልሽ ከሴቶቹ ሁሉ የተባረክሽ ነሽ/2/

ሰላም አልሻለሁ ማርያም ድንግል

እንደ ብስራታዊው እንደ ገብርኤል

ላንቺ የተሰጠሽ ሁለት ድንግልና

አንደኛው በሥጋ ሌላው በጎሊና

ከዓለም ሁሉ ሴቶች ንፅህይት በመሆንሽ

ሰማያዊው ምሥጢር የተገለጸብሽ

የልዑል ማደሪያ ለመሆን ያበቃሽ

የጌታችን እናት በጣም ደስ ይበልሽ

የተነበየላት ሕዝቅኤል ነቢዩ

የተዘጋችው በር ብሎ በራዕዩ

ሳይከፍት ገብቶ ወጣ የሠራዊት ጌታ

ደሞ ከዚያ በኋላ ኖራለች ተዘግታ

ማርያም ስትጎበኛት ወደ ቤቷ ገብታ

ኤልሳቤጥ ዘመረች በመንፈስ ተሞልታ

በመጎፀኗ ያለው ዘለለ በደስታ

እኛንም ትጎብኝን ከጧት እስከ ማታ

ሀይሌ ብርታቴ

ሀይሌ ብርታቴ ክብሬ ሞገሴ(2)

የዘላለሙ የአብርሀሙ ስላሴ(2)

አዝ

ተመረጠች ነፍሴ አንተን ለማወደስ

ከላይ ከአርያም ከስላሴ መቅደስ

በአንድነት ሶስትነትበዙፋኑ ሞልቶ

የሚሳነው የለም ለስላሴ ከቶ

አዝ

ከመንገድ ዳር ልቁም የወደቀ ላንሳ

የተራበ ላብላ የታመመ አልርሳ





እንደ አብርሀም አድርገኝ እንደ ደጉ አባት
ቤቴ እንዲሞላ ያንተ በረከት
አዝ
ጠፈሩን በውሀ በጥበብ የሰራህ
እኔስ ይገርመኛል የስላሴ ስራ
ኑና ተመልከቱት ታምራት ሲሰራ
ሰዎች እልል በሉ ወላድ ሆነች ሳራ
አዝ
አብ አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ወዶናል
ወልድ በተዋህዶ እኛኑ መስሎናል
ሀይሉ ተገለጠ የመንፈስ ቅዱስ
በቅዱሳን አድሮ ሲያድን ሲፈውስ

ዮሃንስ

አይነ ከርም መጥቼ ሳየሁ ዮሃንስ
ብቻውን ያለው ከቶራ ወተት
እየጠባ አደገ በዛ በበርሃ

ከዕቃ ቤቱ ከመቅደሱ መህል
ካህኑ ዘካርያስ ታርጿል
ኤልሳቤት ዮሃንስን ይዛ
ተሰደደች ብቻዋን ተጉዛ

ሲጣራ በህፃን አንደበቱ
አትሰማም አርፋለች እናቱ
ሲርበው ጡቶቿን ይጠባል
ማረፏን ዮሃንስ መች አውቋል

ጌታ እየሱስ ከእናቱ ጋር
ሆኖ መጣለት ደመናን
ተቆኖ ዮሃንስ ፊራ ተሸሸገ
አያውቅም ሰው ብቻውን ያደገ

ድንግል ማርያም ዮሃንስን ልትወስድ
ለመነች ልጇን ልታስፈቅድ
ጌታም አላት በረሃ ነው የሚያድገው
ስራውም መንገድ ጠራጊ ነው

ማርያም እንወድሻለን

ማርያም እንወድሻለን/2/
ስለወለድሽ የህይወት ምግብን
ማርያም እንወድሻለን
..... አዝ.....
ድክመቴን አትይ.....ማርያም
በሀጢያት መወደቄን.....ማርያም
ተስፋዬ አንቺ ነሽ .....ማርያም
እስከለተሞቴ .....ማርያም
.....አዝ.....
ላልከዳሽ ምያለሁ .....ማርያም
ከስርሽ ላልጠፋ .....ማርያም
ገፀ በረከቴ .....ማርያም
የህይወቴ ዋስትና .....ማርያም
.....አዝ.....,.
የምእመናን ውበት .....ማርያም
ዘውድ አክሊላቸው .....ማርያም
ድንግል አንቺ እኮ ነሽ .....ማርያም
የመንገድ ስንቃቸው .....ማርያም
.....አዝ.....
ምስክር ነኝ ለአንቺ .....ማርያም





እንደኑብያቱ .....ማርያም

ስጦታ መሆንሽን .....ማርያም

ለአዳም ልጆች ሁሉ .....ማርያም

.....አዝ.....

ሞገስና ፀጋ .....ማርያም

በጌታ ፊት ያለሽ .....ማርያም

ዋስ ጠበቃችን ነሽ.....ማርያም

እንዴት ነበር ያኔ .....ማርያም

ጌታን ስትወልጂ .....ማርያም

የእረኞቹ ደስታ .....ማርያም

የመላእክት ዝማሬ .....ማርያም

ይኩነኒ በከመ ትብሌለኒ

ይኩነኒ በከመ ትብሌለኒ/2/

አለች የእኛ እናት በትህትና በስጋም በነፍስም ንፅህት ናትና/2/

አለች የእኛ እናት በትህትና ድንግል በክልዔ ንፅህት ናትና/2/

የአዳም ቃል ኪዳን መፈፀሚያው ሲደርስ

ላከው ገብርኤልን ወደ ቤተ መቅደስ

በእግዚአብሔር ሀሊና ተሰላ የነበረች

ከሰማይ የመጣ ቃሉን ተቀበለች

ዳግሚት ሰማይ አርያም ሆነች

ይደረግ ብላ በትህትና ተቀበለች

ማርያም ሆይ አትፍሪ ብሎ እያረጋጋት

ካንች የሚወለደው መድኃኒት ነው አላት

ወንድ ስለ ማላውቅ ይሄ እንዴት ይሆናል

ብላ ጠየቀችው ድንግልን ደንቋታል

ከሴቶች መሐል አንች ልዩ ነሽ

በህግ ሳይሆን በድንግልና ትወልጃለሽ

ህይወት ሊቀዳባት አድሯልበማህፀኑዋ

አይኖርም ከእንግዲህ የሐዋንመርገሟ

በአዲሱ ኪዳን አዲስ ብስራታችን

ምክንያተ ድህነት አለች እናታችን

ቃልህ ይፈፀም ይደረግ ብላ

ታምር ተሰማ እየሩሳሌም ናዝሬት ገሊላ

እጅግ አስገረመን የገብርኤል ዜና

የዘዘካርያስ ከቶ አይደለምና

የተመረጠችው የደረሰው ብስራት

አለምን ከመሞት ከመርገሟ ዋጀች

ከሴቶች መሐል አንች ልዩ ነሽ

በህግ ሳይሆን በድንግልና ትፀንሻለሽ

ኪዳነ ምህረት እመቤት

ኪዳነ ምህረት እመቤት እመቤት/2/

ነይልን ነይልን ካለንበት/2/

ከሰማያት በላይ ካለው ከማደሪያሽ /2/

ዝማሬ ከሞላው ከዘላለም ቤትሽ

የምድር ፍጥረታት ማርያም ማርያም ሲሉሽ/2/

የቃል እናት እመቤቴ ነይ በሰረገላሽ /2/

ከፀጥታ ወደብ ከፍቅር አውድማ /2/

ከሰላሙ መንደር ከእውነት ከተማ

ሰአሊ ለነ ቅድስት ውዳሴ ሲሰማ /2/

ከሚካኤል ከገብርኤል ጋር ነይልን ከራማ /2/

ዘርፋፋው ቀሚስሽ ይውረድ ከሰማያት/2/

እንባችን ይታበስ ባንቺ አማላጅነት

አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር 

ጽዮን ዝማሬ ተሞላ ነፍሳችን /2/

ንዒ /3/እንበል እንደ አባቶቻችን /2/

ፍጥረታት ሊድኑ በአማላጅነትሽ /2/

የዘላለም ኪዳን አማኑኤል ሰጠሽ

ትውልድ ይህን አምኖ ብጽዕት ይሉሻል/2/

እናቴ መመኪያዬ ምርኩዜ ሆነሻል /2/

የልብንሲያዋዩሽ ሰምተሽ ዝም አትይም /2/

ችግረኛን አይቶ ልብሽ አይጨከንም

ከዓይን ጥቅሻ ፈጥነሽት ደርሽለታለሽ /2/

ከሀዘን ከመከራ ታሳርፊዋለሽ /2/

ሁሉም ነገር ሆነ

ሁሉም ነገር ሆነ በግሸን ማርያም

በደብረ ከርቤ በጊሸን ማርያም

በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉም ነገር ሆነ

መስቀሌን በመስቀል - በግሸን ማርያም

እንዳለ በቃሉ - በግሸን ማርያም

በግሸን አደረ - በግሸን ማርያም

ግማደ መስቀሉ - በግሸን ማርያም

ክርስቲያኖች ሁሉ - በግሸን ማርያም

እንዳዝ ከደጅዋ - በግሸን ማርያም

ትኖራለችና -በግሸን ማርያም

ድንግል ከነልጅዋ - በግሸን ማርያም

በገነት መስሎ - በግሸን ማርያም

ጌታ ያስቀመጠው - በግሸን ማርያም

ዙሪያሽ ገደል ሁኖ - በግሸን ማርያም

አንድ መግቢያ ያለሽ - በግሸን ማርያም

ግሸን ደብረ ከርቤ - በግሸን ማርያም

የታቦር ተራራ - በግሸን ማርያም

ሁነሽ የተመረጥሽ - በግሸን ማርያም

የመስቀል ማደሪያ - በግሸን ማርያም

እንማፀናለን - በግሸን ማርያም

ከደጅሽ ላይ ሆነን - በግሸን ማርያም

ባንቺ አማላጅነት - በግሸን ማርያም

ጌታ እንዲለመነን - በግሸን ማርያም

ክብሬ_ነው

ክብሬ ነው ክብርህን መናገሬ

ፅድቄ ነው ፍቅርህን መመስከሬ

ጌታዬ አምላኬ እልሃለው/2/

ስጠራህ ሳመልክህ እኖራለሁ/2/

አይቼ የእጅህን ተአምራት

ሰምቼ የቃልህን ትምህርት

ሆኛለሁ ምስክር ለአዳኝነትህ

ሥጋን ተዋሕደህ ለኛ መገለጥህ/2/

ተከተልኩ ሁሉን ነገር ንቄ

መድሃኒት መሆንክን አወቄ

ከመልካሟ ቤትህ ተጠልያለሁ

የእጅህን በረከት ካንተ እጠግባለሁ/2/

እርፍ ይዤ ላላርስ ወደ ኃላ

እያየሁ መረቤን ስትሞላ

እመካብሃለሁ ባንተ መድኀኔ

አምላኬ ነህና የምትራራ ለኔ

አንድነት የቅድስት ኪዳነምህረት መንፈሳዊ ማህበር 

አባቴ ነህና የምታስብ ለእኔ

ቸርነት ምህረት ከበዛልኝ

ለስምህ ውዳሴ ቅኔ አለኝ

ክብሬና ሞገሴ አንተ ነህ ጌታ

ተመስገን ተመስገን ጠዋትና ማታ /2/

ውበት ነሽ

ውበት ነሽ ለቤቴ ለኑሮዬ ፋና

ድንግል ሆይ አትለይኝ ብቻዬን ነኝና

በሃዘን ጠቋቁራ ተከፍታለች ገፂ

አጎንብሻለሁኝ አፈሬ በለምዒ/2/

ወልቋል ከራሴ ላይ የብርሃን ልብሴ

ሃብቴ አንቺ ብቻ ነሽ ያለሽኝ ሞገሴ/2/

ለአምላኬ የማቀርበው አጣሁ በጎ ስራ

ነፍሴ ተጨነቀች በምግባሬ መርራ/2/

ጥላሸቱ በዝቶ ተዳፍኖኗል ጎጆዬ

ብርሃን የለውም ካልበራ ሻማዬ/2/

የምታመንበት አንዳች ነገር የለኝ

በነፍስም በስጋ ሁሉ የጎደለኝ/2/

እጠባበቃለሁ የእጅሽን በረከት

እቤቴ ላይ አርፎ እስክባረክበት/2/

የጓዳዬ ክብር የቅጥሬ ድምቀት ነሽ

ዓይኔን የምትሞይው በመቅረዜ በርተሽ/2/

የዕልመት ጭላንጭል ጠፍቷል የለም ዛሬ

የብርሃን እናት ስላለች በበሬ/2/